# የብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች በዓል
# የህገ-መንግስታችን ነፀብራቅ!

ሰዒድ አህመድ 11-24-14

የኢ.ፌዴሪ ህገ-መንግስት የጸደቀበት ህዳር 29 የኢትዮጵያ ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች ቀን ተብሎ በአገር አቀፍ ደረጃ በድምቀት እንዲከበር የተወሰነው የፌዴሬሽን ምክር ቤት ሚያዚያ 21 ቀን 1998 ዓ.ም ባካሄደው ሶስተኛው የፓርላማ ዘመን አንደኛ አመት ሁለተኛ መደበኛ ስብሰባ ላይ ነበር።

የፌዴሬሽን ምክር ቤት የኢትዮጵያ ብሄሮች ብሄረሰቦችና ህዝቦች ቀን በየዓመቱ ህዳር 29 ቀን እንዲከበርና በዋነኝነት የወሰነው የአገራችን ህዝቦችም ተመካክረውና ፈቅደው የጸደቁት ህገ-መንግስት ያስገኘላቸውን ጥቅሞች እንዲያስቧቸው ለማድረግና በቀጣይ ማከናወን የሚገባቸውን ተግባሮች ላይም መምከር እንዲችሉ ለማድረግ ታቅዶ ነው።

በአገራችን የመጀመሪያው የብሄሮች ብሄረሰቦችና ህዝቦች ቀን በ1999 ዓ.ም በፌዴሬሽን ምክር ቤት አዘጋጅነት በአዲስ አበባ ሲከበር መሪ ቃሉም **"ሕገ-መንግስታዊ ቃል ኪዳን የአብሮነታችን መገለጫ ነው"** የሚል ነበር። ሁለተኛው በዓል ደግሞ በደቡብ ኢትዮጵያ ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች መዓከል በሆነችው ሀዋሳ ላይ በድምቀት ሲከበር መሪ ቃሉም **"ልዩነታችን ውበታችን ውበታችን አንድነታችንና ጥንካሬያችን ነው"** በሚል ተከብሯል።

ሶስተኛው የብሄሮች ብሄረሰቦችና ህዝቦች ቀን በ2001 ዓ.ም በኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት አዘጋጅነት በአዲስ አበባ ሲከበር መሪ ቃሉም **"ዴሞክራሲየዊ አንድነታችን በማጠናከር ልማታችንን እናፋጥናለን"** የሚል ነበር። አራተኛው በዓል ደግሞ በድሬደዋ አስተዳደርና አጎራባች ክልሎች (ኦሮሚያ፣አፋር፣ ኢትዮጵያ ሶማሌ፣ እና ሀረሪና ድሬደዋ ከተማ አስተዳደር) በአንድነት አዘጋጅነት በድሬዳዋ በ2002 ዓ.ም የተከበረ ሲሆን መሪ ቃሉ **"መቻቻል ለዴሞክራሲያዊ አንድነትና ልማት"** የሚል ነበር፡፡

አምስተኛው ከአለም የፌዴራል ቀን ጋር በማያያዝ በ2003 ዓ.ም በአዲስ አበባ የተከበረ ሲሆን መሪ ቃሉም **"የኢትዮጵያ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ሕዝቦች እጅ ለጅ ተያይዘን የአገራችንን ህዳሴ ወደ ማይቀለበስበት ደረጃ እናደርሳለን"** የሚል ነበር፡፡ ስድስተኛው በትግራይ ክልላዊ መንግስት አዘጋጅነት በመቀሌ በ2004 ዓ.ም ሲከበር መሪ ቃሉ **"ሕገ መንግስታችን ለብዝሀነታችን ለአንድነታችንና ለሕዳሴችን"** የሚል ነበር፡፡

ሰባተኛው የብሄሮች ብሄረሰቦችና ህዝቦች ቀን ደግሞ በአማራ ክልላዊ መንግስት አዘጋጅነት በባህር ዳር በ2005ዓ.ም የተከበረ ሲሆን መሪ ቃሉም **"ብዙም አንድም ሆነን በመለስ ራዕይ በሕገ-መንግስታችን**

**ለሕዳሴያችን**" የሚል ነበር፡፡ ስምንተኛው ዙር ደግሞ በሶማሌ ክልላዊ መንግስት አዘጋጅነት በጅግጅጋ የ2006 ዓ.ም የተከበረ ሲሆን መሪ ቃሉም "ሕገ-መንግስታችን ለህዳሴያችን" የሚል ነበር፡፡

ዘጠንኛውና የዘንድሮ የብሄሮች ብሄረሰቦችና ህዝቦች ቀን በዓል በቤንሻንጉል ጉምዝ ክልላዊ መንግስት አዘጋጅነት በአሶሳ ለማክበር የአሶሳ ነዋሪዎችና የክልሉ መንግስት እንግዶቻቸውን ለመቀበል ሽር ጉድ በማለት ላይ ይገኛሉ። የዘንድሮው የብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ቀን በዓል "**በህገ-መንግስታችን የደመቀው ኢትዮጵያዊነታችን ለህዳሴያችን**" በሚል መሪ ቃል ይከበራል።

የብሄሮች ብሄረሰቦችና ህዝቦች ቀን በዓል የብሄር፣ ብሄረሰቦችንና ህዝቦችን እኩልነት፣ አብሮ የመኖርና የመቻቻል እሴቶቻችንን ከማጎልበት ባሻገር ህዝቦች በአገራችን እየተመዘገበ ያለውን እድገት ማስቀጠል በሚቻልበተ ሁኔታዎች ላይ ይመክራሉ። ስምንተኛው የብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች ቀን በዓል የተከበረባትን ጅግጅጋንና የዘንድሮው የብሄሮች ብሄረሰቦችና ህዝቦች ቀን የሚከበርባትን አሶሳን ስንመለከታቸው የአገራችን ከተሞች እድገት የተመጣጠነ በአገራችን እየተመዘገበ ያለው እድርትም ፍተሃዊ መሆኑን ማሳያ ሊሆኑ ይችላሉ።

በየትኛውም ኮርነር ያሉ የአገራችን ከተሞች እንዲህ ያሉ ትላልቅ ኢቨንቶችን ማስተናገድ መቻላቸው የአገራችን እድገት በመአከል ብቻ ሳይሆን በሁሉም አካባቢዎች ስለመሆኑ ጥሩ ማረጋገጫ ይመስለኛል። በአገራችን እየተመዘገበ ካለው እድገት ፍተሃዊ የሃብት ክፍፍል መኖሩን ከሚያሳዩ ነገሮች መካከል የተመጣጠነ የከተሞች እድገት ዜጎች ከዕድገቱ ተጠቃሚ መሆናቸውን የሚያሳይ ነገር ነው።

ጅግጅጋንና አሶሳን የመሳሰሉ ከመሃል አገር በብዙ መቶ ኪሎ ሜትሮች ርቀው የሚገኙ አርብቶ አደር የሚበዛባቸው አካባቢዎች እንዲህ ያሉ ትላልቅ አገራዊ ኢቨንቶችን ማስተናገድ ቀርቶ ለመስክ ስራ የሚወጡ ባለሙያዎች በተገቢው ሁኔታ ማስተናገድ የማይችል ከተሞች ዛሬ ላይ በአስር ሺዎች የሚቆጠሩ ሰዎችን ማስተናገድ የሚያስችል አቅም መፍጠራቸው በከተሞች የመሰረተ ልማት መሟላትን የሚያሳይ ነው።

ይህን ጉዳይ ለዛሬው እዚህ ላይ ላቁመውና ወደ ርዕሰ ጉዳዬ ልመልሳችሁ። የብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች ቀን በዓል እንዲህ ባለ በእኩልነትና በነጻነት ለመከበር የቻለው ጭቁን ህዝቦች ለዘመናት በከፈሉት መሰዋዓትነት ነው። በእልህ አስጨራሽ ትግል አምባገነን ስርዓትን አሽቀንጥረው በመጣል በእኩልነትና በወንድማማችነት ላይ መሰረት ያደረገች አዲሲቷን ዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያን እውን ማድረግ ችለዋል። የኢፌዴሪ የህገ-መንግስት የአዲሲቷ ኢትዮጵያ መሰረት በመሆኑ የፌዴሬሽን ምክር ቤት ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች ቀን ህገመንግስቱ የጸደቀበት ቀን ህዳር 29 እንዲከበር አድርጎ የወሰነው።

የኢትዮጵያ ህገ-መንግስት የህዝቦችን ነጻነት በማረጋገጥ ረገድ ከማንኛውም አገር ህገ-መንግስት በተሻለ ሁኔታ የሚጠቀስ ነው። በህገ-መንግስቱ አንቀጽ 39ኝ ላይ ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች እስከመገንጠል የሚፈቅደውን አንቀጽ አንዳንዶች አገሪቱን ወደመበታተን የሚወስድ ነው በማለት ከህገ-መንግስቱ ላይ

እንዲነሳ ሲወተውቱ ይታያሉ። ይሁንና በተግባር ይህ አንቀጽ በህገመንግስቱ ላይ መካተቱ በተግበር የተመለከትነው በህዝቦች መካከል መተማመን እንዲነግስ ያደረገ አንቀጽ እንጂ አገሪቱን ሲበትናት ወይም ለሁከትና ብጥብጥ ሲዳርጋት አልታየም። ይህ አንቀጽ በአገራችን ዳግም ጭቆና እንዳያንሰራራ ለብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች ዋስትና የሚሰጥ  አንቀጽ መሆኑንም መዘንጋት የለበትም።

በለፉት ሁለት አስርት ዓመታት የአገራችን ህዝቦች በህገ-መንግስቱ ውስጥ የተቀመጡ መብቶቻቸውን ተጠቅመው አንድ የጋራ ፖለቲካዊና ኤኮኖሚያዊ ማህበረሰብ ለመፍጠር ያስቀመጡትን ራዕይ ተግባራዊ ለማድረግ በጋራ ተረባርበዋል። በአገራችን ዘለቄታዊ ሰላም ማስፈን በመቻሉም አለምን ያስደመመ እድገት ማስመዝገብ ተችሏል። አገራችን እያስመዘገባች ያለችው በለሁለት አሃዝ እድገት የህገ-መንግስታችን ውጤት መሆኑን መገንዘብ የሚያስቸግር አይመስለኝም። በእርስ በርስ ጦርነትና ረሃብ ትታወቅ የየነበረች አገር ከአፍሪካ አልፋ በአለም በእድገት መታወቅ የቻለችው በዚህ ህገ-መንግስት ሳቢያ በተገኘ ዘላቂ ሰላም ነው።

የዘንድሮው የብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች ቀን **“በህገ-መንግስታችን የደመቀው ኢትዮጵያዊነታችን ለህዳሴያችን”** በሚል መሪ ቃል የሚከበር ሲሆን በበዓሉ ወቅት በፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ስርዓታችን የተመዘገቡትን ድሎች መለስ ብለን የምንዳስስበትና ስኬቶቻችንን የምናሰፋበት  ለችግሮቻችን መፍትሄ የምናፈላልግበት እንዲሁም ለተጨማሪ ድሎች ማስመዝገብ ጠንክረን ለመስራት ቃል የምንገባበት ይሆናል።

የዘንድሮው በዓል የሚከበረው በህዝቦች ተሳትፎ እየተገነባ ባለው ታላቁ የኢትዮጵያ የህዳሴ ግድብ እየተገነባ ባለበት ክልል መሆኑ በራሱ የሚፈጥረው የልማት ተነሳሽነት በቀላሉ የሚታይ አይሆንም። የታላቁ የኢትዮጵያ የህዳሴ ግድብ የሁሉም ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች አሻራ ያረፈበት ፕሮጀክት በመሆኑ ከኤኮኖሚ ጠቀሜታው ባሻገር ለእኛ ኢትዮጵያዊያኖች የትብብራችንና የአንድነታችን  ማሳያ ነው።

የብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች ቀን በዓል በሚከበርበት ወቅት አገራችን የተያያዘችውን የልማትና የዴሞክራሲ ስርዓት ግንባታ ትግላችንን አጠናክረን በማስቀጠል አገራችንን ከድህነትና ከኋላቀርነት ተላቃ መካከለኛ ገቢ ካላቸው አገሮች ተርታ ለመሰለፍ የምታደርገውን ጥረት ለማፋጠን ቃል የምንገባበት ወቅት መሆን አለበት።

የዘንድሮ በዓል የሚከበረው የመጀመሪያው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዘመን መጠናቀቂያና  እንደመሆኑ በዕቅድ የተያዙት ስራዎችን  ለማሳካት ሁላችንም በሃላፊነት ስሜት የምንረባረብበት መሆን ይኖርበታል። እንዲሁም የቀጣዩን የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ የምናዘጋጅበት ወቅት በመሆኑ የካበትናቸውን ልምዶች በአግባብ በመቀመር አዲስ እቅድ ማዘጋጀት ይጠበቅብናል።

የአገራችን ኢኮኖሚ ባለፉት አስር  ዓመታት በላይ ለተከታታይ ባለሁለት አሃዝ  እድገት ማስመዝገብ ችሏል። አገራችን ይህን እድገት ማስመዝገብ የቻለችው አንዳንድ ጠንካራ ኤኮኖሚያዊ አቅም ኣላቸው

የሚባሉ አገራት ሳይቀሩ  በከፍተኛ ቀውስ ውስጥ በነበሩበት ወቅት ሳይቀር መሆኑ አገራችን የተከተለችው የልማት ፖሊሲዎችና  ስትራቴጅ ምን ያህል ስኬታማ እንደሆኑ የሚያመላክት ነው።

ሌላው መጠቀስ ያለበት ነገር በአገራችን እየታየ ያለው እድገት ሁሉንም የአገራችንን ዜጎችና የአገራችንን አካባቢዎች ያማከለ መሆኑ ነው። በአገራችን የተመዘገበው እድገት ሰፊውን የህብረተሰብ ክፍል መሰረት ያደረገ በመሆኑ ከተገኘው እድገት ሁሉም በየደረጃው ተጠቃሚ እንዲሆን አስችሎታል።

የአገራችን ኤኮኖሚ እድገት መሰረት ያደርገው በተፈጥሮ ሃብት ላይ በተለይ በነዳጅ ላይ ሃብት ላይ የተንጠለጠለ ባለመሆኑ የፍተሃዊነት ችግር የለበትም። የአገራችን ኤኮኖሚ መሰረት ያደረገው ግብርና ላይ መሆኑና ፈጣን የሆነው እድገትም በዚሁ ዘርፍ መሆኑ በሁሉም የአገሪቱ ክልሎች  ተመጣጣኝ የሆነ የእድገት እንዲኖር አድርጎታል።

የብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች ቀን በዓል የሚያሳየው  የፌዴራል ስርዓቱ በህዝቦች መፈቃቀድ ላይ የተገነባ መሆኑን  የሚያስመሰክሩበት አንዱ መድረክ ነው። እንዲሁም ይህ በዓል  በአገራችን የብሔር ጭቆና፣ አፈናና አድልዎ ዳግም ላይመለስ መቀበሩን በድጋሚ የሚያረጋግጡበት እንዲሁም  የድህነትና ኃላቀርነት ዘመን እንዳይመለስ ለማድረግ ጠንክረው ለመስራት ቃል የሚገቡበትም ወቅት ጭምር ነው።

የብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች ቀን በዓል በሚከበርበት ጊዜ ሁሉ የኢትዮጵያ ህዝቦች ለዚህ ሁሉ ድልና ስኬት መሰረት የጣለው ህገ-መንግስታችንን የማክበርና የማስከበር ሃላፊነት እንዳለብን ከዚህ ቀደሙ ሁሉ ወደፊትም ቃላችንን የምናድስበት ቀን ይሆናል።

ባለፈው አመት በዓሉ በጅግጅጋ በተከበረበት ወቅት አንዳንድ አስተያየት ሰጪዎች ይህ አካባቢ የኦጋዴን ብሔራዊ ነጻነት ግንባር /ኦብነግ/ የተባለው አሸባሪ ሃይል ከአንዳንድ ሃይሎች ጋር በመተባበር የኢትዮጵያን ሶማሌ ክልልን በሃይል ለመገንጠል በሚል በዜጎች ላይ የከፋ በደል ሲፈጽም የቆየበት አካባቢ በመሆኑ በዓሉ የጸጥታ ችግር ይፈጠራል የሚል ስጋት አድሮባቸው ነበር። ይሁንና እውነታው እንዲህ ካለው አስተሳሰብ ፈጽሞ የተለየ ነበር።  የክልሉ ህብረተሰብ የኦብነግን የጥፋት ድርጊት በማውገዝና አሸባሪውን ሃይል ለህግ አጋልጦ በመስጠት  ክልሉ ፍጹም ሰላማዊና የተረጋጋ  እንዲሆን በማድረግ በዓሉ በደማቅ ሁኔታ እንዲከበር አድርጓል።

ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ስርአታችን ገና ታዳጊ ቢሆንም እጅግ ስኬታማ የሆነ ውጤቶችን በማስመዝገብ በትክክለኛ መንገድ ላይ መሆኑን በተግባር አስመስክሯል። አንዳንድ ጽንፈኛ ፖለቲከኞች ለህዝቦች ካላቸው ንቀትና ጥላቻ በሚመነጭ እኛ እናውቅልሃለን ስሜት የኢትዮጵያን የፌዴራል ስርዓት የጎሳ ፌዴራሊዝም (Ethnic Federalism) የሚል ስያሜ በመስጠት ስኬታማ እንደማይሆንም ቢተነብዩም ትንብያቸው

ሊሰምርላቸው አልቻለም። የተመኙት መበታተንና የጦርነት አደጋ በኢትዮጵያችን አልታየም። ይልቁንም ኢትዮጵያ በቀንዱ ብሎም በአፍሪካ የሰላም ተምሳሌት በመሆን ለጎረቤት አገራት ህዝቦች መጠለያ፣ ለመንግስቶቻቸው ደግሞ ሰላም አፈላላጊ ለመሆን በቅታለች።

የኢፌዴሪ ህገ-መንግስት በጣም ዘመናዊ ከሚባሉ ህገ-መንግስቶች የሚመደብ ነው። ሁሉንም የዜጎችን የሰባዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች መከበር በግልጽ የሚደነግጉ አንቀጾችን አካቷል። በክፍል አንድ ውስጥ በህገ-መንግስታዊ ጥበቃ የሚደረግላቸው ሰብአዊ መብቶች በአስራ አምስት አንቀጾች ተዘርዝረው ተቀምጠዋል።

ህገ-መንግስቱ የዜጎችን በህግ ፊት ያለምንም ልዩነት እኩል የህግ ጥበቃ እንደሚደረግላቸው ደንግጓል። በዘር፣ በብሔር ብሔረሰብ፣ በቀለም፣ በጾታ፣ በቋንቋ፣ በሃይማኖት፣ በፖለቲካ፣ በማህበራዊ አመጣጥ፣ በሃብት፣ በትውልድ ወይም በሌላ አቋም በሰዎች መካከል ልዩነት እንደማይደረግና ሁሉም ሰዎች እኩል ተጨባጭ የህግ ዋስትና የማግኘት መብት እንዳላቸው በግልጽ ያስቀምጣል። ይህም ባለፉት ሁለት አስርት ዓመታት በተግባር ተረጋግጧል።

ከዚህ በተጨማሪ የኢፌዴሪ በህገ-መንግስት ሰብአዊ መብትን በተመለከተ ያስቀመጠው አብይ ድንጋጌ በሰብዕና ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎችን የሚመለከት ነው። በህገ-መንግስት አንቀጽ 28 ላይ እንደተመለከተው አገራችን ባጸደቀቻቸው አለም አቀፍ ስምምነቶችና በሌሎች የኢትዮጵያ ህጎች በሰው ልጅ ላይ የተፈጸሙ ወንጀሎች ተብለው የተወሰኑትን የሰው ዘር የማጥፋት፤ ያለፍርድ የሞት ቅጣት እርምጃ የመውሰድ፣ በአስገዳጅ ሰውን የመሰወር ወይም ኢ-ሰብአዊ የድብደባ ድርጊቶችን በፈጸሙ ሰዎች ላይ ክስ ማቅረብ እንደሌሎች ወንጀሎች በይርጋ እንደማይታገድና በህግ አውጭም ሆነ በማንኛውም የመንግስት አካል በምህረት ወይንም በይቅርታ እንደማይታለፉ ተሰምሮበታል። ይህ ድንጋጌ አገራችን ለዜጎች ሰብአዊ መብቶች መከበር እስከምን ድረስ ጠንካራ አቋም እንዳላት የሚያመለክት ነው።

የኢፌዴሪ ሕገ-መንግሥት በክፍል ሁለት ስር የዴሞክራሲ መብቶችን በተመለከተ 16 አንቀፆች የተከፋፈሉ ድንጋጌዎች አስፍሯል። በእነዚህ አንቀፆች አማካኝነት የአገራችን ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ዴሞክራሲያዊ መብቶቻቸው ሕጋዊ እውቅና አግኝተዋል። በዚህም መሠረት የዜጎች የአመለካከትና ሃሳብን በነፃ የመያዝና የመግለፅ መብት፣ ከዚሁ ጋር በተያያዘም የፕሬስና የሌሎች የመገናኛ ብዙኃን እንዲሁም የሥነ-ጥበብ ፈጠራ ነፃነት ተረጋግጧል። ባለፉት ሥርዓቶች ይደረጉ የነበሩ የቅድመ ምርመራ እንቅስቃሴዎች በሕገ-መንግሥቱ አማካኝነት ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ተወግደዋል። በመሆኑም ዛሬ በአገራችን እጅግ በርካታ ፓርቲዎች በህጋዊ መንገድ ይንቀሳቀሳሉ።

እንዲሁም ዜጎች መረጃዎችን የማግኘት መብታቸውም ሕግ-መንግሥታዊ እውቅና አግኝቷል። የምንግሥት ሚዲያም የተለያዩ አስተሳሰቦችን በሚያስተናግድበት መንገድ እንዲመራ ሕገ-መንግሥት ያዝዛል። ይህም በመገናኛ ብዙሃኖች ተግባራዊ ሆኗል። ይሁንና አንዳንድ በነጻው ፕሬስ ስም የተቋቋሙ ጋዜጦችና መጽሄቶች ህገ-መንግስቱ የሰጣቸውን መብት ያለአግባብ በመጠቀም አገርንና ህዝብን ጥቅም በሚጎዳ መልኩ ሲንቀሳቀሱ ይታያሉ።

ሕገ-መንግሥታችን ዜጎች የመሰብሰብ፣ ሰላማዊ ሰልፍ የማድረግ ነፃነት እና እንዲሁም በሕጋዊ መንገድ ለሕጋዊ ዓላማ የመደራጀት መብት እንዳላቸው ይደነግጋል። ዜጎች በአገራቸው ውስጥ በነፃነት የመዘዋወር መብት እንዳላቸው፣ በፈለጉ ጊዜ ከአገር ወጥተው የመመለስ መብታቸው የተከበረ መሆኑን ሕገ-መንግሥቱ ያስቀምጣል።

ሕገ-መንግሥቱ የዜግነትን መብት ያስከበረ ሲሆን የጋብቻ፣ በግል እና የቤተሰብ መብቶችንም በአዲስ መሠረት ላይ እንዲገነቡ አድርጓል። ሕገ-መንግሥቱ ሴቶች ከወንዶች ጋር እኩል መብት እንዳላቸው ከማረጋገጡም በላይ ሴቶች በታሪክ በበታችነትና በልዩነት በመብታቸው የደረሰባቸውን ሁኔታ ግምት ውስጥ በማስገባት ይህንኑ ለማረም የሚያስችል የልዩ ድጋፍ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ያዝዛል። ይህም በተግባር ላይ ውሎ ዛሬ ላይ በአንዳንድ መስኮች ሴቶችና ወንዶች እኩል ደረጃ ላይ ማድረስ ተችሏል።

ሕገ-መንግሥታችን የህፃናት መብትን በተመለከተም ዝርዝር ድንጋጌዎችን አካትቷል። ህፃናት በሕግ የተቀመጡ መብቶቻቸውን ተጠቅመው ብቁ ዜጎች ሆነው እንዲያድጉ ሕገ-መንግሥታዊ ዋስትና ተደርጎላቸዋል። የሀገራችን ወጣቶች በሕገ-መንግሥቱ ላይ የሰፈሩ መብቶች ሁሉ ተጠቃሚዎች ናቸው። ያለፉት ወጣት ትውልዶች የታገሉላቸው የዴሞክራሲ እና የሰብዓዊ መብቶች ዛሬ የሚገኘው ትውልድ የሚያጣጥማቸው ድሎች ናቸው። ዛሬ ላይ ወጣቱ የሚያስበው ስለጦርነት፣ ሞትና ስደት ሳይሆን ስለልማትና እድገት ሆኗል።

የዜጎች የመምረጥና የመመረጥ መብትም ሕገ-መንግሥታዊ እውቅና አግኝቷል። የአገራችን ብሔሮች ብሔረሰቦችና ሕዝቦች የራሳቸውን ዕድል በራሳቸው የመወሰን ያልተገደበ መብታቸውም ለመጀመሪያ ጊዜ እውቅና ያገኘው በዚህ ሕገ-መንግሥት አማካኝነት ነው። የሀገራችን ብሔሮች ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ራሳቸውን በራሳቸው የማስተዳደርና በክልል እና በፌዴራል አስተዳደሮች ውስጥ ሚዛናዊ ውክልና የማግኘት መብታቸው እንደተከበረ ተደንግጓል። ሕገ-መንግሥቱ ከፌዴራል ሥርዓቱ ለመውጣት የሚሹ ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች የሚከተሉትን ሕጋዊ ሥርዓትም በግልፅ አስቀምጧል። ይህን ህጋዊ መስመር የሚከተል ማንኛውም መገንጠል የሚፈልግ አካል በህገመንግስቱ በሚያዘው መሰረት በአግባብ የሚስተናገድበት ሁኔታ ተቀምጧል።

በአጠቃላይ ሕገ-መንግሥቱ የአገራችን ዜጎች ዴሞክራሲያዊ መብቶች ተከብረው ዜጎች በነፃነት የሚኖሩባት አዲሲቷን ኢትዮጵያን ለመፍጠር መሠረት ጥሏል። ዛሬ በአገራችን በፖለቲካዊ አስተሳሰብ መደራጀት የተለመደ ተግባር ሆኗል። በሕጋዊ መንገድ የተመዘገቡ በርካታ የፖለቲካ ፓርቲዎች በአገራችን በነጻነት ይንቀሳቀሳሉ። ሃሳብን የመግለፅ መብት በመረጋገጡ የግል ሚዲያ እየተስፋፋ ይገኛል። የተለያዩ ሃሳቦችም በነፃነት ይንሸራሸራሉ።

በሃይማኖት ምክንያት የሚደርሱ ተፅዕኖዎች ተወግደው ሁሉም ሃይማኖቶች በእኩልነት እየተስተናገዱ ይገኛሉ። ዛሬ በአገራችን መንግስታዊ ሃይማኖትም ሆነ ሃይማኖታዊ መንግስት የለም። ይህ በመሆኑም ሃይማኖቶች ሁሉ ተከባብረውና ተቻችለው የሚኖሩባት አገር መመስረት ተችሏል። በዜጎች የንብረት መብት ላይ የተጣለው ገደብ ተነስቶ ዜጎች ያልተገደበ ሃብት ማፍራትና የመጠቀም መብታቸውን በተግባር ላይ

አውለዋል። የሀገራችን ሠራተኞች ተደራጅተው ለመብታቸው የመታገልና ጥቅማቸውን የማስከበር መብታቸውን አረጋግጠዋል። እንግዲህ እነዚህ ሁሉ የህገ-መንግስታችን ቱርፋቶች ናቸው።

ከላይ ለመጥቀስ እንደሞከርኩት በአገራችን የታየው ልማትና እድገትም ቢሆን የህገ-መንግስታችን ውጤት ነው። በዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ መሠረት አገራችን በታሪኳ አከናውናው የማታውቃቸውን እጅግ ግዙፍ የሆኑ ባለ ቢሊዮን ዶላር ወጪ የሚጠይቁ ፕሮጀክቶችን መገንባት ጀምራለች። ለአብነት ያህል ከአፍሪካ ቀዳሚ የሆነ የውኃ ኃይል ማመንጫ ግንባታ፣ የባቡር መስመር ዝርጋታ፣ ዘጠኝ ግዙፍ የስኳር ፋብሪዎችና የማዳበሪያ ፋብሪካዎች ግንባታዎች እንዲሁም በመንገድ ግንባታ፣ በቴሌኮሙዩኒኬሽን ዝርጋታ ወዘተ አገልግሎት የታዩት ዕድገቶች እጅግ ከፍተኛ ከመናቸውም ባሻገር የአገራችንን ዕድገት ወደ ፊት በማራመድ ረገድ ጉልህ ድርሻ እንደሚኖራቸው እሙን ነው።

መንግስት የከተማ ነዋሪዎችን ህይወት ለመለወጥ  እንዲቻል የተለያዩ ፖሊሲና ስትራቴጂዎችን ነድፎ ተንቀሳቅሷል። በዚህም በርካታ የከተማ ነዋሪዎች ተጠቃሚ የሆኑበትን የአነስተኛና ጥቃቅን ኢንተርፕራይዞችን መስፋፋት  ሳቢያ በርካታ ዜጎች ስራ እንዲፈጠሩላቸው በመሆኑ ገቢያቸው እንዲጨምር በመደረጉ የከተማ ነዋሪዎች ህይወት መለወጥ ችሏል።

በዜጎች መካከል ፍተሃዊ የሃብት ክፍፍል እንዲኖር ለማድረግ በከፍተኛ ድጎማ  የመኖሪያ ቤቶችን  በተለያዩ የአገሪቱ ከተሞች የመኖሪያ ቤቶችን በመገንባት  በእጣ እያከፋፈለ ይገኛል። ይህም በርካታ የከተማ ዝቅተኛና መካከለኛ ገቢ ያለቸው ነዋሪዎች የቤት ባለቤት የሆኑበት ሁኔታን ማየት ይቻላል።

በትምህርትና በጤናው ዘርፍ መንግስት እያከናወናቸው የሚገኙት ተግባራት በበርካታ አንጸባራቂ ድሎች የተሞሉ ናቸው። ባለፉት ጥቂት አመታት በርካታ የመንግስት ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ተከፍተዋል። የአገራችን  የመንግሥት ዩኒቨርሲቲዎች ቁጥር ብቻ ከ33 በላይ ለማድረስ ተችሏል። በአገራችን  የአንደኛ ደረጃ የትምህርት ሽፋን ከ95 በመቶ በላይ እንዲሁም የተማሪዎች ቁጥርም  ከ22 ሚሊዮን በላይ ማድረስ ተችሏል። ይህ ቁጥር ምን አልባት ከብዙ የአፍሪካ አገሮች የህዝብ ብዛት  የሚበልጥ ሆኖ እናገኘዋለን። ይህ የሚያሳየው አገራችን በጥቂት አመታት ውስጥ ምን ያህል የተማረ የሰው ሃይል ሊኖራት እንደሚችል መገመት የማያስቸግር አይመስለኝም። በጤናው ዘርፍም አገራችን ከፍተኛ ስኬት ያሳየችበት ነው። በአንዳምዶቹ ዘርፎች አገራችን የሚሌኒየም ዴቨሎፕመንት ጎሉን ቀድማ በማሳካት እንደአብነት የምትጠቀስ አገር መሆን ችላለች። ይህ ሁሉ ስኬቶች የአገራችን ህገ-መንግስት ወጤቶች ናቸው።

በህገ-መንግስታችን የጸደቀው የፌዴራል ስርዓታችን ውጤታማ የሆነው በህዝቦች መካከል መከባበርና መቻቻል እንዲሰፍን በመደረጉ ነው። የሕግ የበላይነትም ሆነ የተቋማት አደረጃጀት እና አሠራር መረጋጋት ሊረጋገጥባቸው ከሚችሉ ጉዳዮች አንዱ ሕገ-መንግሥት ነው። ሕገ-መንግሥቱ በፌዴራሉ ሥርዓት ውስጥ ሕዝቦች በመካከላቸው ስለሚኖር ዝምድና እና የጋራ መስተጋብር መሠረታዊ መርሆዎችን ያስቀምጣል።

የፌዴራሉን ሥርዓት ሚዛናዊ በሆነ መንገድ ለማስተዳደር የሚያስችሉ የሥልጣን ክፍፍል ቁልፍ መርሆዎችንም ያስቀምጣል። እነዚህ መርሆዎች ሲከበሩ በርግጥም የሕግ የበላይነት ይረጋገጣል። የሕግ የበላይነት በተከበረበት ሁሉም ወገኖች ድምፃቸው የሚሰማበትና ውሳኔ በማሳለፍ ሂደት ላይም ተሳታፊ በሚሆኑበት ሁኔታ መቻቻል ሊጎለብት ይችላል።

እንግዲህ የዘንድሮው የብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች ቀን “በህገ መንግስታችን የደመቀው ኢትዮጵያዊነታችን ለህዳሴያችን” በሚል መሪ ቃል የሚከበር ሲሆን በበዓሉ ወቅት በፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ስርዓታችን የተመዘገቡትን ድሎች መለስ ብለን የምንዳስስበትና ስኬቶቻችንን የምናሰፋበት ለችግሮቻችን መፍትሄ የምናፈላልግበት እንዲሁም ለተጨማሪ ድሎች ማስመዝገብ ጠንክረን ለመስራት ቃል የምንገባበት ይሆናል።

የኢፌዴሪ ሕገ-መንግሥት ገና ከመግቢያ ጀምሮ በሕዝቦች መካከል መቻቻል እንዲኖር የሚያመላክት ሃሳብን አስፍሯል። የሕገ-መንግሥቱን መሠረታዊ ዓላማ በሕገ-መንግሥቱ ዙሪያ የተሰባሰቡት ሕዝቦች አንድ የጋራ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያ ማኅበረሰብ እንዲፈጥሩ፣ በህዝቦች መካከል መከባበርና መቻቻል እንዲሰፍን ማድረግ ነው።